# ጸሎት ማለት ምን ማለት ነው?

ጽሎት ማለት በሰዋሰው ትርጉም "ጸለየ" ለመነ፡ ጠየቀ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን መለመን መጠየቅና ክርስትያናዊ ፍላጎቶችን መግለጽ ማለት ነው። በምስጥራዊ ትርጉሙ ጸሎት ማለት ከኢግዚአብሐር ጋር መነጋገር ማለት ነው።የሚጸልይ ሰው ብቻውን የሚነጋገር ሳይሆን ከኢግዚአብሐር ጋር ይነጋገራል ማለት ነው። "ለምኑ ይሰጣችሁማል ፈልጉ ታገኙማላችሁ" (ማተ 7፡7) ጸሎት ከኢግዚአብሐር ጋር የአእምሮ ግኑኝነት ነው። ጸሎት በበጉና በአውሬው መካከል የሚደረግ መንፈሳዊ ጦርነት ክርስታንያዊ ውጊያ ኢንደሆነ ከእግዚአብሐር ቃል እንረዳለን። "መጋደላችን ከደምና ከስጋ አይደለምና፡ ከአለቆችና ከባለስጣናት ከክፉት መንፋሳውያን ጋር ነው ኢንጂ።" (ኤፊ፡ 6፡12) በጸሎት አፈጻጸም ስራት አቸናፊው እግዚአብሐር ነው ተዋጊው ሰይጣንና የድል ሓይል እንዲሰጠው የሚፈልገው ስው ይገኝበታል። መንፈሳዊ በሆነ ጦርነት ሁልጊዘ አችናፊው ኢግዚአብሐር ነው። ጸሎት ሰማይንና ምድርን የያዘውን እግዚአብሐርን ክንድ ማንቀሳቀስ ነው። የአንድ ምእመን የሃይማኖቱ ደረጋጃ የሚለካው በጸሎት ጽናት የኢግዚአብሐርን ክንድ ማንቀሳቀስ ሲችል ነው። በሃይማኖታችን የመጽናታችን ምልክቶች ከሖኑት መካከል አንዱና ዋናው በጸለት መጽናት መቻላችን እንደሐነ ከእነ ቅዱስ ጴጥሮስ ህይወት መማር እንችላለን። እነ ቅዱስ ጴጥሮስ በገተስማኒው የጸሎት ጊዘ ባያንቀላፉ ኖሮ ቀራንዮ ሳይድርሱ



ባልተበተኑ ነበር።

ጸሎት በሚጸልዩ ሰዎች የአገልግሎት ደረጃ፤ ብዛትና የጸሎት ህይወት ልምድ ብሁልት ይከፈላል።

1. የግል ጸሎት፡ ማንኛውም በየትኙውም ቦታ ለብቻው ሆኖ የሚጸልየው ነው። ክርስቶስ የግል ጸሎት ምን አይነት እንደሆነና እንዴት መፈጸም እንዳለበት በተግባር አሳይቶናል።
2. የማህበር ጸሎት፡ በቤተክርስትያን ለጸሎት መስባስብ ካህናትና መመናን በጋራ ሆነው የሚጸልዩት ነው፡ "..ሁለት ወይም ሶስት በስሜ በሚሰባሰቡበት ቦታ እገኛለሁ" ማቴ18፡19-20

(ጸጋ እግዚአብሄር ከመምህር ቀለም ወርቁ ኪዳነማርያም 1996)